# በልማት ትብብር እና በሰብአዊ እርዳታ ፕሮግራሞች ውስጥ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ማስቆምን በተመለከተ የDAC ምክረ ሐሳብ፡ የመከላከልና ምላሽ የመስጠት ቁልፍ ምሰሶዎች

ይህ በኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) የታተመው የእንግሊዝኛው ዋና ቅጂ ኦፊሴላዊ ያልሆነ ትርጉም ነው። ይህ ህትመት በሚከተሉት ድርጅቶች በተናጠል የተተረጎመ ነው፡- Social Development Direct እና Translators without Borders ። የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) ይህን ትርጉም አላጸደቀም ፣ ለዚህ ትርጉም ጥራት እና ትክክለኛነትም ተጠያቂ አይደለም።

**የOECD ልማት እርዳታ ኮሚቴ (DAC)**

በትምህርት ፣ በሥራ ስምሪት እና በስራ ፈጠራ [OECD / LEGAL / 0398]የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ ምክር ቤቱ የሰጠውን አስተያየት በተመለከተ; የሙስና አደጋን ለመቆጣጠር የልማት ትብብር ተዋንያን ምክር ቤት [OECD/LEGAL/0431 በሕዝባዊ ሕይወት ውስጥ የሥርዓተ ፆታን እኩልነት በተመለከተ ምክር ቤቱ የተሰጠው አስተያየት [OECD/LEGAL/0418] እና የሰብአዊ ዕርዳታ DAC ምክሮች
ልማት- ሠላም ጥመረት በተመለከት[ [OECD/LEGAL/5019] ] ; **በማክበር**

በልማት እና በሰብአዊ ዘርፎች የፆታ ብዝበዛን እና ጥቃትን በመዋጋት እና በG7 ልማት ሚኒስትሮች በተደረገው ዓለም አቀፍ ድጋፍ ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ ላይ የዊስለር መግለጫን በተመለከተ ለ DAC ታይድዋተር የጋራ መግለጫን ፣ **በማክበር**

በ 2018 የለንደን ከጥቃት ጥበቃ መከላከያ ጉባኤ ላይ በዓለም አቀፍ የእርዳታ ዘርፍ ውስጥ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመቋቋም ለጋሾች የሰጡትን ቃል **በማክበር**

የሥርዓተ ጾታ እኩልነትና የሰብአዊ መብቶች ልዩ ልዩ ገጽታዎች በተለይም በአለም ዐቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በአለምአቀፍ መሳሪያነት የተጣሉ መሰረቶችን፤ በዋነኛነት በዐለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች የተካተቱት መሰረተ ሐሳቦች፤ የጄኔቫ ስምምነቶችንና ተያያዥ ፕሮቶኮሎችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው የዐለም አቀፍ የሰብዐዊነት ሕጎች አንቀጾች፤ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ላይ የአለም አቀፍ ቃል ኪዳን፤ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊና በባህላዊ መብቶች ላይ የአለም አቀፍ ቃል ኪዳን ፤ በህጻናት መብቶች ላይ የተባበሩት መንግስታት ስምምነቶች፤ በሴቶች ላይ ያለውን ሁሉም አይነት መድልኦ ለማስወገድ የተባበሩት መንግስታት ስምምነት፤ የሴቶችን ጥቃት ለማስወገድ የተባበሩት መንግስታት የአቋም መግለጫ ሰነድ (A/RES/48/104) ፤ በተባበሩት መንግስታት እና ግንኙንት ባላቸው ሠራተኞች የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ዕርዳታና ድጋፍ ላይ የተባበሩት መንግስታት ሁሉን ዐቀፍ ስተራቴጂ (A/RES/62/214) ፤ የተባበሩት መንግስታትን ሥራ የሚሰሩ አጋር ድርጅቶችን ጨምሮ የወሲባዊ ብዝበዛና በድል ስለመፀማቸው ማስረጃ ያልቀረበባቸው ክሶች ላይ የተባበሩት መንግስታት ፕሮቶኮሎች ፤ በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ ያለውን ሁሉም አይነት ጥቃት ለመከላከልና ለማስወገድ ጥረቶችን ለማጠናከር የ2018 በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ፡ ወሲባዊ ትንኮሳ (A/RES/73/148)፤ እንዲሁም በሴቶችና በቤት ውስጥ ሠራተኞች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን መከላከልና መዋጋት ላይ የአውሮፓ ምክር ቤት ስምምነትን **በማክበር**፤

የ2030 አጀንዳ ለዘላቂ ልማት ፤ በህዝብና ልማት ላይ የ1994 የድርጊት ፕሮግራም የዐለም አቀፍ ስብሰባበ ፤ የ1995 የቤጂንግ ድንጋጌዎች እና አራተኛው የሴቶች የዐለም ስብሰባ ተግባራዊ መድረክ እንዲሁም ከነዚህ ቀጣይ የሆኑ የግምገማ ስብሰባዎች ውጤት ሠነዶችን ጨምሮ ከተባበሩት መንግስታት አንጻር አግባብነት ያላቸው ቃል የተገባላቸው የፖለቲካዊ ውሳኔዎችን **በማክበር፤**

የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ና ትንኮሳ ተግባራት አግባብነት ያላቸውን የዐለም አቀፍ ደረጃዎችንና ህጎችን በድፍረት የሚጥሱናፍፁም ተቀባይነት የሌላቸው መሆናቸው ፤ ፤ በባህርያቸው በግለሰብና በማህበረሰብ ላይ ከህሊና የማይጠፋ እጅግ አሰቃቂ ገጠመኝ የጉዳት ተጽእኖ ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በእርዳታ ሰጪዎችና በአጋሮቻቸው የተፈፀሙ ከሆነ ደግሞ የዐለም አቀፉን ዕርዳታ ሰጪ ማህበረሰብ አንድነትና ራሱን ዕርዳታውን ተዓማኒነት ወደ ጥያቄ የሚያስገባው መሆኑን **እውቅና በመስጠት** ፤

የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን ለማሳካት የአለምን ጥረትን በተለይም የዘላቂ ልማት ግብ-5፡ "የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ማሳካትን እና ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለሥልጣን ማብቃትን" የሚያዋርድ መሆኑን፤ **እውቅና በመስጠት፤**

ለጋሾችና አጋሮቻቸው የድርጅቶቻቸውን የአሰራር ባህልና ልማድ የወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት ና ትንኮሳ መከላከል ወይም ሳይከሰት አሰቀድሞ የመከላከልና ጉዳቱን የመቀነስ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ሲያቅታቸው የሥልጣን ሚዛናዊነት የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ጉድለት ጎልቶ በሰፈነበት እና ግጭት ባጠቃው በቀላሉ ጉዳት የመድረስ ስጋቶች የተባባሰባቸው አካባቢዎችን ጨምሮ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ትንኮሳ እንደሚጨምር **እውቅና በመስጠት**

ለጋሾችና አጋሮቻቸው የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ አጋጣሚዎችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ቅንጅትና ቅንብር እንደሚያስፈልጋቸው፤ የድርጅቶችን ባህል ለውጥና ተጠያቂነትን ለመምራት ጠንካራ የለጋሾች መድረክ መገንባት፤ ሰለባ ለሆኑና ከጉዳት ለተረፉ ምላሽ መስጠትና ጥቃት አድራሾች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ፤ በሁሉም የዕርዳታ ዘርፍ የዐቅም ግንባታን ማጠናከር ፤ የሴቶችንና ልጃገረዶችን ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሴቶች መብቶች ድርጅቶች እና በሴቶች የሚመሩ ድርጅቶች ዋና ድርሻ እንዳላቸው መገንዘብ፤ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት በአለምዐቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ጥረቶች የሴቶችንና ልጃገረዶችን የማዕከላዊ ድርሻ አስፈላጊነትን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም በአለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪ ተዋናዮች በኩል የሚፈጸሙትን የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ አዝማሚያዎችንና የሚመጡ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች አግባብ ካላቸው ከአለምአቀፍ ደረጃዎች ጋር ማጣጣምን **እውቅና በመስጠት**

የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ለመከላከል በሚወሰዱ ልዩ እርምጃዎች ላይ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ሪፖርትን ጨምሮ እነዚህን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተባበሩት መንግስታት ጥረቶች ማለትም፡- የ (2017) አዲስ አቀራረብ ፤ ከነዚህ ጋር የተያያዙ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ቡለቲኖች፤ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ

ልዩ እርምጃዎች (2003)፤ መድልኦን፣ ትንኮሳን፣ ወሲባዊ ትንኮሳን እና ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም (2003)፣ ያልተገባ ባህርይ እና ተግባርን ሪፖርት ለሚያደርጉ ከሚደርስባቸው በቀል ጥበቃ እና በህግ የተፈቀደ ብርበራና ምርመራን ትብብር ማድረግ (2017)፣ ውሳኔ ቁጥር 1325 (2000) እና ተከታታይ ውሳኔዎች እስከ ውሳኔ 2242 (2015) ድረስ ያሉትን ጨምሮ ሴቶች፣ ሰላምና ደህንነትን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት የፀታው ምክር ቤት ውሳኔዎች፤ በወሲባዊ ትንኮሳ ላይ ሞዴል ፖሊሲ (2018)፤ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ልዩ አስተባባሪ የተሰራ አስፈላጊ ሥራ ይኸውም የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት (ጾ.ብ.በ) እና የወሲባዊ ትንኮሳን (ጾ.እ) ላይ የተባበሩት መንግስታት ምላሽን ማሻሻል፣ በተባበሩት መንግስታት ሰለባ ለሆኑ የመብቶች ጠበቃ፣ ለሰለባዎች የተባበሩት መንግስታት የአደራ ፈንድ፣ በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ እና በእያንዳንዱ አባል ሀገሮች መካከል በፈቃደኝነት የተደረገ የጋራ ሰነድ፣ የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት (ጾ.ብ.በ) እና የወሲባዊ ትንኮሳን (ጾ.እ) በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ላይ በተባበሩት መንግስታት ሥራዎች አመራር ዙሪያ፣ በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት (ጾ.ብ.በ) እና በወሲባዊ ትንኮሳን (ጾ.እ) መከላከል ላይ የሲቪል ማህበረሰብ አማካሪ ቦርድ እና ለታላቁ የጥቅም ልውውጥ አጀንዳ ለሰብአዊነት (2016)፣ እና የአካል ጉዳተኞችን በሰብዓዊነት ድርጊቶች ማካተት ቻርተር (2016) **እውቅና መስጠት ፤**

በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ላይ በኤጀንሲዎች (በድርጅቶች) መካከል ያለ የቋሚ ኮሚቴ መርሆዎችና ዝቅተኛ የሥራዎች ደረጃዎች (MOS-PSEA)፣ በጥራትና በተጠያቂነት ላይ ዋናው የሰብዓዊነት ደረጃዎች (CHS)፣ እንደ አስፈላጊ የዐለም አቀፍ ደረጃዎች እንደሆኑ **አውቅና መስጠት**

ከጉዳት የተረፉ እና ሰለባ የሆኑትን ማዕከል ያደረገ አቀራረብ ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል እና ወሲባዊ ትንኮሳ ፖሊሲዎች ጋር የማቀናጀት አስፈላጊነት ከሚከተሉት አራት የመመሪያ መርሆዎች ጋር የሚሄዱ መሆናቸውን ማለትም 1) ደህንነት 2) ሚስጥራዊነት 3) ማክበር እና 4) በተባበሩት መንግስታት እና ግንኙንት ባላቸው ሠራተኞች የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ዕርዳታና ድጋፍ ላይ የተባበሩት መንግስታት ሁሉን ዐቀፍ ስልት/ስትራቴጂ (A/RES/62/214) እንደተገለፀው አድሎአዊነት የሌለበት መሆኑን፣ እንዲሁም ከጉዳት የተረፉ ልጆች ደህንነት፣ ጥበቃ እና ጤንነት ማረጋገጥን **እውቅና በመስጠት**

የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ሚዛናዊ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት ባለመኖር ምክንያት ስር የሰድዱ ናቸው፣ በተለይም ሥርዓተ ጾታ እኩልነት አለመኖር ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን እና ሌሎች ዓይነቶች ጥቃቶች እና መድልኦዎች እዲባባሱና እንዲጨምሩ ማድረጉን **እውቅና መስጠት**

የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ የሰብዓዊ መብቶችን ጥቃትና ጥቃትን ሊይዝ ይችላል፤ ስለሆነም የሰብዓዊ መብቶችን ማስተዋወቅ፣ መጠበቅ እና ማክበር የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ መከላከልና መዋጋትን ማዕከል ያደረግ መሆኑን **እውቅና መስጠት** በልማት ትብብር እና በሰብአዊነት ዕርዳታ ላይ የሰብዓዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አቀራረብ መሰረታዊ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ሴቶችና ህጻናት እንዲሁም ባላቸው ማንነት የመድልኦ ስጋት ላለባቸው ለምሳሌ አካል ጉዳተኞች፣ ጾታ፣ የሥርዓተ ጾታ ማንነት፣ ዘር፣ ነገድ፣ ዕድሜ፣ ሀይማኖትን ጨምሮ ማናቸውም ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖች ልዩ ትኩረት ያስፈልጋል፡፡

**I. በዚህ ሰነድ ለተጠቃለለው ምክረ-ሃሳብ ዓላማ ብቻ የሚከተሉት የቀል ውይም ሀረግ ፍቺዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ** ተስማምተዋል :

ሀ.**ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (ለጋሽ ተብሎም በሚጠራው)**እንደ ይፋዊ የልማት ዕርዳታ (ODA) ተብለው የሚመዘገቡትን በመንግሥት በኩል ገንዘብ ለመስጠት ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ወይም ሌሎች የመንግሥት ወይም የግል ድርጅቶችን ያመለክታል ፡፡

ለ. ***ሥራን የሚተገብሩ አጋሮች*** የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ወይም ሌሎች የመንግሥት ኤጀንሲዎችን ፣ እንዲሁም በእርዳታ ፕሮጀክቶች ወይም መርሃግብሮች ወይም በእርዳታ ገንዘብ ተቀባይ የግል ሴክተር ድርጅቶች በመተግበር ላይ በሚሳተፉ የዓለም አቀፍ ልማት አጋሮችን ልክ እንደ ታዳጊ አገሮች መንግሥታት ፣ የአካባቢ ባለሥልጣናትን ጨምሮ የሕዝብ አካላት፣ የአካባቢ ባለሥልጣናትን ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን ፣ የሠራተኛ ማኅበራትን ፣ ሁለገብ ልማትና ሰብዓዊ ድርጅቶችን እና ዕቃዎች እና አገልግሎቶች አቅራቢዎችን ያመለክታል፡፡

**II.** የዚህ የልማት ድጋፍ ኮሚቴ ምክረ ሀሳብ (DAC ) ዓላማ ሊደግፍ ፣ ሊመራ ፣ ሊያበረታታ የሚችል አጠቃላይ ማዕቀፍ ማቅረብ እና የልማት ድጋፍ ኮሚቴ የሆኑና ያልሆኑ አባላትን (ከዚህ በኋላ **"ተከታዮች")** በመለገስ አቅማቸው ለመርዳት፣ ከዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጋር የሚጣጣም እና ብሔራዊ ሕጎችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ባለድርሻ አካላትን የበለጠ አጠቃላይ እና የተጣጣሙ እርምጃዎችን እንዲተገብሩ ለመርዳት እንዲሁም ጾታዊ ብዝበዛ እና ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት እንደሆነ ይስማማል፡፡ ይህም ከጉዳት በሕይወት የተረፉትን እና ተጎጂ ሰለባዎችን በማስቀደም ፣ የድርጅታዊ ባህላዊ ለውጥን መደገፍ ፣ አቅም መገንባት ፣ ተጠያቂነትን ማጎልበት እና የዓለም አቀፍ የእርዳታ ዘርፍ ታማኝነትን ማጎልበትንም ይጨምራል ፡፡

**III. ተከታዮች የ** የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ **ን** መከላከል እና ምላሽን ለማጠናከር ፣ አደጋን ለመቆጣጠር እና የተረፉትን እና ተጎጂዎችን ለመደገፍ እና ለመጠበቅ የልማት ትብብር እና የሰብአዊ ድጋፍ ስርዓቶችን ማቋቋም ወይም መከለስ ይመክራሉ። **ተከታዮች** እነዚህ ስርዓቶች በአለም አቀፍ የልማት ኤጄንሲዎቻቸው እና በእርዳታ አሰጣጥ እና / ወይም አያያዝ ላይ ባከናወኗቸው ተግባራት ሁሉ አጋሮቻቸውን በሚተገብሩ በቂ ሀብቶች ላይ ተመስርተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው ፡፡ **ተከታዮች** እነዚህን ስርዓቶች በማቀናበር ወይም በማሻሻል (በመከለስ) እና አግባብ ላላቸው ግዴታዎች ፣ ሚና (ድርሻ) ዎች እና ሃላፊነቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-

1.***ፖሊሲዎችን እና የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃዎችን ማዘጋጀት እና በዓለም አቀፍ እርዳታ አቅርቦት ላይ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ላይ የአደረጃጀት ለውጥ እና አመራር ለማጎልበት መፈልግ፡፡*** ለዚህ ውጤት ተከታዮች እንደአግባቡ መሆን ያለባቸው፡-

ሀ. በአሳታፊነት ***ያለ አድሎአዊነት ፣የሴቶች ምልመላ እና የሙያ እድገትን ማበረታታትን*** ፣ ጨምሮ በጾታ ሚዛናዊ የሥራ አካባቢዎችን እና ዕድሎችን ፣ ከፍተኛ አመራር ውስጥ እና በሁሉም ድርጅቶች ውስጥ ወሲባዊ ብዝበዛ እና አላግባብ መጠቀምን እና ምላሽን ጋር በተያያዙ ግቦች ፣ እሴቶች ፣ ባህሪዎች እና ተስፋዎች ላይ ውጤታማ በሆነ እሴት ላይ የተመሠረተ አመራር እና መመሪያን በማሻሻል የተሻሻለ የድርጅታዊ ባህል እና ደረጃዎችን (ደንቦችን) ማሳደግ።

ለ. ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጋር በተያያዝ ቀጣይነት ያለው የከፍተኛ አመራር,ተሳትፎ እና የአመራር ቁርጠኝነት አዎንታዊ የድርጅታዊ ባህል እና ደንቦችን ለመቀየር ወይም ለማቆየት ጉልህ ሚና መጫወቱን፡፡ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ጉዳዮች እንዴት እንደሚፈቱ በመደበኛ የከፍተኛ አመራር ደረጃ ውይይቶች በማካሄድ፣ ***እንዲሁም*** የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ለመከላከል የሚውል ለዚሁ የተለየ የድርጅታዊ አቅም እንዲኖርና ከ ሰፊው ***ሰብአዊ መብቶች እና የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ቁርጠኛ አቋሞች ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ፡***

ሐ. በብቃት የሚተገበሩ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ***መከላከል እና ምላሽ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን ፣ ስትራቴጂዎችን እና የሥራ እቅዶችን*** ማዘጋጀት፣ ግቦችን እና ደረጃዎችን ማውጣት፣ የተጣጣመ አቀራረብን ተዛማጅ የሥራ ፍሰቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ይደግፉ ፡፡ በእነዚህ ፖሊሲዎች ውስጥ ተከታዮች ለወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ተገቢ ምላሽ ለመስጠት አለመቻላቸው ሊታለፍ እንደማይችል ግልጽ ማድረግ አለባቸው፣ መከላከል እና ምላሽ ምንም ጉዳት አለማድረስን ያቀደ ከአደጋ የተረፉ እና ተጎጂዎችን ማዕከል ባደረገ አቀራረብ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ፡፡

መ. የየወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ***ለመከላከል እና ለመዋጋት ግልጽ የሆኑ መመዘኛዎችን እና ደንቦችን*** ን የሚያወጡ የሥነ ምግባር ደንቦችን ማዘጋጀት ወይም በይፋ መገኘታቸውን እና ለሠራተኞች እና ለከፍተኛ አመራሮች በተከታታይ ቁልፍ የሥራ ዑደት ጊዜያት ሁሉ (የምልመላ እና የዲሲፕሊን ሂደቶችን ጨምሮ) ፣ ለ ስራ

ዝግጅትም ሆነ ግዳጅን በመወጣት ወቅትመ ጊዜ ፣ በአፈፃፀም አስተዳደር መዋቅሮች እና በአመራር እሴቶች ውስጥ ማዘጋጀት፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የስነምግባር እና የስነምግባር ደረጃዎች ከአስፈፃሚ አጋሮች ጋር መጋራት እና አግባብነት ላላቸው ለአከባቢው ማህበረሰቦች አግባብነት ባላቸው ቋንቋዎች እና ቅርፀቶች በንቃት መገኘት አለባቸው ፡፡

ሠ. ለሰራተኞች **መቼ እና ለማን** ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ፣ እና በሚስጥራዊነት ፣ ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችንማዕከል ያደረገ እና ሥነ ምግባራዊ ጥንቃቄ የተሞላበት ምላሽ ለመስጠት የሪፖርት እና የምላሽ ፕሮቶኮሎችን ማዘጋጀት ፡፡ የተሻሻሉ የተጠያቂነት ስልቶች ወደ ብዙ የወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ሪፖርቶች ሊያመሩ እንደሚችል በመገንዘብ ሰራተኞቹ ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃት የመፈጸምን ክስተቶች ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ፣ ምላሽ ለመስጠት እና ክትትል ለማድረግ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ በመያዝ ፣ ከበቀልም የሚጠብቅ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡

ረ. ጥሰቶች እና የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶች ከሚያስከትሏቸው ነገሮች ጎን ለጎን በሁሉም **የሕብረት ሥራ ስምምነቶች እና የገንዘብ መሣሪያዎች** (ለምሳሌ ፣ ኮንትራቶች ፣ ድጋፎች ፣ የመግባቢያ ማስታወሻዎች) ውስጥ ደረጃዎችን ፣ አሰራሮችን ፣ መስፈርቶችን እና / ወይም አስገዳጅነት ቃላትን ያካትቱ ፡፡

2. **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን ማዕከል ያደረገ የምላሽ እና የድጋፍ ስልቶችን ማዘጋጀት ወይም መደገፍ፡፡** እነዚህ ስልቶች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችንልምዶች ፣ መብቶች ፣ ፍላጎቶች የሪፖርት ፣ የምርመራ እና የምላሽ ስርዓቶች** ማእከል ባሉበት እና ሊጋሾችን እና የሚተገበሩ አጋሮች በወቅቱ ምላሽ በመስጠት እና በሂደቱ ውስጥ በሕይወት **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን**በመደገፍ እንዲሁም በመከላከል **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን**ማዕከል ባደረገ ሂደት የፆታ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል እና ምላሽ መስጠት:: ይህ አካሄድ ሴቶችንና ሕፃናትን ጨምሮ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን እንዲሁም ለምሳሌ በአካል ጉዳተኝነት ፣ በፆታ ማንነት እና በጾታ ዝንባሌ ፣ በዘር ፣ በጎሳ ፣ በዕድሜ ወይም በሃይማኖት ላይ በመመርኮዝ ለመድልኦ አደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን**ማዕከል ያደረገ አካሄድ ሰብአዊ መብቶችን እንዲሁም አክብሮትን ፣ ግላዊነትን ፣ ደህንነትን እና አድልዎ ያለማድረግን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

**ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን"**እርዳታ ለማቅረብ መቼ እና እንዴት ስልቶች ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችሉ ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችን እና መመሪያዎችን በማካተት ለሁሉም የማህበረሰብ አባላት የሚገኙትን ውጤታማ ፣ ግልፅ እና ቀላል **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችንየቅሬታ ዘዴዎችን** ማካተት፡፡ የቅሬታ አሰራሮች ፣ ማህበረሰብን ጨምሮ የተመሰረቱ ስልቶች፣ ከተወሰነ አካባቢያዊ እና ባህላዊ አውዶች ጋር ተጣጥመው ከአከባቢው አመራሮች ጋር በመተባበር እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ተገቢ ከሆኑ እና ከከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር በጋራ የሚደገፉ በመሆን ሊዳበሩ እና ሊተገበሩ ይገባል፡፡

ሐ.ልክ እንደ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የአከባቢ የሴቶች ድርጅቶች፤ የአካባቢ እና ብሄራዊ መንግስታት ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝ; እና የአካባቢ ባለሥልጣናትን ጨምሮ የህዝብ አካላት ያሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን"**ጨምሮ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ሪፖርት ለሚያደርጉ የተቀናጀ እና ደህንነቱ የተጠበቀ **ምላሽ እና ጥበቃ** ማቅረብ፡፡ ተከታዮች ከጉዳት ለተረፉ እና ለተጎጂ ሰለባዎች ዋነኛ (ቁልፍ) ባለድርሻ አካላትን እና ለሪፈራል የአገልግሎት አቅራቢዎችን ጨምሮ ዕርዳታ ፣ መፍትሄ እና ድጋፍ ፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን ከፍተኛ በሆነ መልኩ በጋራ የሚደገፉ አስፈላጊ የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት የምያስፈልጉ መመሪያን እና ዝቅተኛ ደረጃዎችን ማዘጋጀት አለባቸው ፡፡

መ.አሁን ያሉትን **አካባቢያዊ አገልግሎቶች እና አውታረ መረቦችን ለማጠናከር እና በጾታ ላይ ከተመሠረቱ ጥቃቶች እና ከልጆች ጥበቃ አገልግሎቶች ጋር ቅንጅትን** እንዲሁም ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመፍታት መፈልግ፡፡ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እና በአካባቢ ደረጃ የሚፈጸም ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ምላሾችን ለማጠናከር **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን**ማዕከል ያደረገ አቀራረብ ወደ ሰፋ ያሉ ጥረቶች መቀናጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ጥረቶች የሪፈራል አገልግሎቶች ጥራትንና ተደራሽነትን ለማሻሻል፣ እንዲሁም **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎች** የሆኑትን የማግለል ሰጋቶችን ለመቀነስ አላማ ማድረግ አለባቸው፡፡

3. **ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል የድርጅት ሪፖርትና ምላሽ ሰርዓቶች እንዲሁም የአሠራር ሒደቶች መመስረት (ማዘጋጀት)፡፡** እነዚህ ሥርዓቶችና የአሠራር ሒደቶች መያዝ ያለባቸው፡-

ሀ. ለለጋሾችና ፈፃሚ አጋሮች የጥቃት አጋጣሚዎችንና እና ክሶችን በአግባቡ ለመያዝ (ለማስተዳደር) የሚያስችሉ የተደራጁ ስራዎችንና ዘዴዎችን ጨምሮ አግባብ ያለውና አወዱን ያገናዘበ፣ **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎች**የሆኑትን ማዕከል ያደረገ **የውስጥ ቅሬታና ምርመራ የአሰራር ሂደቶች፡፡** ያለማስረጃ ክስ የቀረበባቸው ተጠርጣሪ ወንጀለኞች የግል መብት እንዳላቸው በመገንዘብ ለእነሱ ደጋፊ የሆኑ እንዳግባቡ ገለልተኛ የሆነ የአሰራር ዘዴ መፈለግ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ቀላል፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተደራሽ፣ አውዱን ያገናዘበ፣ ከባህሉ አንጻር አግባብነት ያላቸው **የሪፖርትና ቅሬታ ዘዴዎች** እነዚህም የተቀናጀ የምላሽ ጥረቶችን ወጥነትን ለማረጋገጥ ሚስጥራዊ እና ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦችና ማህበረሰቦች አጋጣሚዎችን ማንነታቸው ሳይታወቅ ሪፖርት ማድረግ የሚችሉባቸው ናቸው፡፡ ይህ ለድርጅት ሰራተኞች፣ አጋሮች፣ የእርዳታ ተቀባዮች፣ የተቀባዮች ቤተሰቦቻቸው እና ማህበረሰቡ እንዲሁም በሀገሩ የህጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፎች መሰረት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተገቢነት ያለው የአካባቢውን እና የአገሩ መንግስታትን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ገለልተኛ የሆነ መረጃ የመስጠት ስርዓት ሊያካትት ይችላል፡፡

ሐ. **ጉዳት ለደረሰባቸው** ወይም መረጃ የሚሰጡትን ጨምሮ ሪፖርት በሚያደርጉ ላይ ከሚደርስ በቀል ለመጠበቅ የጥበቃ ፖሊሲ በማስቀመጥ፤

መ.የአካባቢውን **ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በልማት ትብብር እና ሰብዓዊ ዕርዳታ በኩል የአካባቢውን አቅም ፣** የህግ የበላይነት፣ የፍትህን ተደራሽነትን እና የላቀ ተጠያቂነትን እንዲኖር መደገፍ

ሠ.የውስጥና የውጪ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተጠናከረ ግልጽ የሆነ የመከላከል ሥራን በመደገፍ፣ **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን** ደህንነትንና ፍላጎትን፣ እና ከመረጃ ማጋራት ጋር የተያያዘ **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን** የሆኑትን መብት ግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ የማግኛ መንገድን ማሻሻል፣ ሚስጥራዊነትን፣ ይሁንታን፣ የወደፊት በሰል የጥቃት አጋጣሚዎችን ለመከላከል ለተረፉትና ሰለባ ለሆኑት ጥበቃ የስጋት ዳሰሳ ጥናት፣

ረ. የሠራተኞችን ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንዳስፈለጊነቱ የማባረር፣ የማገድ፣ እና ሌሎች እርምጃዎችን ለመውሰድ ፖሊሲዎችንና የአሠራር ሒደቶችን ማረጋገጥ፣ ይህ ደግሞ ሁለቱን ዘዴዎችንና የማስተዳደር ሀላፊነቶችን ለማረጋገጥ በተመሳሳይ የማካተት ባህልን፣ እምነትን፣ተጠያቂነትንና ግልጽነትን ለማስፈንና ለማሳደግ መልካም ተሞክሮን ለማስተዋወቅ እና ለትምህርትና ለመሻሻል ሽልማቶችና ማበረተቻዎችን መጠቀም ያስፈልጋል ፡፡

ሰ. ለሠራተኞች የስነምግባር መርሆዎችን **ሲጥሱ** ቅጣቶችን **ለማድረግ** ግልጽ የሆነ የመግባቢያ ዘዴዎችን መጠቀም

ሸ. ወንጀለኞችን ከሥራ ቅጥር ለመከላከል (ለምሳሌ እንደገና መቅጠር፣ ዝውውር ወይም ዕድገት) ውጤታማና ግልጽ **ምልመላ፣ የሥራ አፈጻጸም አስተዳደር፣ ሪፈራል**

**ልምምዶች፤** ዕጩዎችን ለመለየት የሚያስችል የተሻሻሉ ዘዴዎችን ጨምሮ፤ የጀርባ ማንነታቸውን፣ ስለ ዕጩዎች ዋቢ ምስክሮች፣ ለቀደመ ስነምግባር ከወንጀል ነፃ ማስረጃ ማወቂያ ሰርዓት መዘረጋት፤

4. **ሥልጠና ማካሄድ፣ ግንዛቤ ማሳደግ እና የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ላይ መነጋገር** እነዚህ እርምጃዎች በቂና ቀጣይነት ያለው ግብዓት ይፈልጋሉ፤ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ. **ውጤታማ ተግባቦት፤** በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት (ጾ.ብ.በ) እና ወሲባዊ ትንኮሳ (ጾ.እ) ላይ ምላሽ መስጠት ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የህግ ድንጋጌዎችን መረጃ መስጠትን ጨምሮ ፤ የሚመለከታቸው ሀገራዊ ህጎች፣ የለጋሽ ድርጅቶች ደረጃዎች፣ እና የስነምግባር ሕጎች፤ አስፈላጊና የሚጠበቅ የለጋሾች አስተዳደር፣ ሠራተኞች፣ የግል ሴክተሩን ጨምሮ ተግባራዊ ሥራ የሚሰሩ አጋሮች፣ እና ጥቃቶችን ሪፖርት ለማድረግ እንዴት የቅሬታ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል ናቸው፡፡

ለ. በደረጃዎች፣ የስነምግባር ሕጎች፣ ቅሬታዎችን የማመልከት ዘዴዎችና ስነምግባርን ሪፖርት የማድረግ፣ እንዲሁም ደረጃዎችን የመጣስ አንድምታዎች፣ የፀረ-በቀል ፖሊሲዎችን ጨምሮ ውጤታማ የባህል ለውጥ እና ደህንነት፣ መተማመን እና የተከበረ የሥራ አካባቢ ላይ ለአስተዳዳሪዎች እና ሠራተኞች **መደበኛ ሥልጠና እና የአቅም ግንባታ፤** ሥልጠና እና ከፆታ እኩልነት ሥልጠናጋር መያያዝ ወይም መጣጣም ይኖርባቸዋል፤ በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል መደብ ላይ የተሰየሙ ዋና ሠራተኞች በተቻለ መጠን ሙያዊ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፤

ሐ. **ግንዛቤ የማሳደግ ፣ ትምህርታዊና መከላከልጥረቶች** ወይም ፕሮግራሞች ከሚተገብሩ አጋሮች ጋር የእርዳታ ተቀባዮችን እና የአካባቢው ሕዝብ ስለመብቶቻቸው የተገነዘቡ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ፣ ሪፖርት የማድረግ ዘዴዎች፣ ለተገልጋዮች ያሉ ድጋፍ አገልግሎቶች በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ምላሽ የመስጠት ፕሮግራሞችን በመቀየስ እና እንደአስፈላጊነቱ ሰፋ ያሉ ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ የዕርዳታ ተጠቃሚዎች እና የአካባቢው ሕዝቦችን መሰረታዊ ፍላጎቶችን ስለማካተቱ ለማረጋገጥ እነርሱን ማማከር ያስፈልጋል፡፡ ይህ በአካባቢው የተመሰረቱትን ድርጅቶች፤ የሴቶች መብቶች ድርጅቶችን፣ በብሔራዊ የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል አውታረመረብ እና ዘዴዎችን ጨምሮ የአቅም ግንባታ እና ስልጠና ሊጨምር ይችላል፤ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በዋናው መስሪያ ቤት እና፣ በመስክ ቢሮዎች፣ በተግባር ከሚሰሩ አጋሮች እና አካባቢየዊና ብሔራዊ መንግስታት መካከል መከፋፈል ይኖርባቸዋል፣ እንዲሁም ደህንነት እና አግባብ ያለው በሚሆን ጊዜ ከሴቶች እኩልነት እና ያለአድሎ በሚሰሩ የህዝብ አካላትን፣ የአካባቢ ባለስልጣናትን ጨምሮ በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ጋር ግንኙነት ካላቸው ጋር መከፋፈል ይኖርባቸዋል፡፡

5. **ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ዐለምአቀፍ ቅንጅትን ማረጋገጥ፡፡** ለዚህ ውጤታማነት ተከታዮች ማድረግ ያለባቸው፡-

ሀ. **ግልጽ ደረጃዎች እና የሚጠበቁብ ሥራዎችን ለማቀድ ያሉትን እርምጃዎች ከዐለም አቀፉ ለጋሾችና ፈፃሚ አጋሮች ጋር ማቀናጀትና ማጣጣም፤** ይህም **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን**መሰረታዊ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠትና እና በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት (ጾ.ብ.በ) እና ወሲባዊ ትንኮሳ (ጾ.እ) ለመከላከል እና ምላሽ ላይ አጠቃላይ እርምጃ እስከ መውሰድ ድረስ፤

ለ. በዲኤሲ አባላት **ቃል የተገቡትን ማካተትና** በጥራትና ተጠያቂነት ላይ ዋና ሰብአዊ ደረጃዎችን (ሲኤችኤስ)፣ በበይነ ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ ዝቅተኛ የሥራ ደረጃዎች (ኤምኦኤስ-ፒኤስኢኤ)፣ አግባብ ያላቸው የኦኢሲዲ እና ዲኤሲ ምክረ ሃሳቦችን ጨምሮ በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ያሉትን የፖሊሲ መሰረቶች፤ እና ሌሎች አግባብ ያላቸውን በአለም ዐቀፍ ደረጃ ቃል የተገቡትን በለጋሾች ቃል የተገቡትን ጨምሮ ማለትም የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ትንኮሳ በዐለምአቀፍ ሴክተር በለንደን የ2018 የጥበቃ ስብሰባ ጨምሮ፤

ሐ.በDAC አባላት፣ **በአጋሮች እና በዐለም አቀፍና በብሔራዊ ባለሙያዎች የተባበሩት መንግስታት በተለይ የበይነ-ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ (IASC) እና በተባበሩት መንግስታት ሥርዐት** ለትብብር ዋና አስፈጻሚ ቦርድ (CEB) መካከል በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል እና ምላሽ መስጠት ላይ የቅርብ ትብብር እና አብሮ መስራትን ማረጋገጥ ከጉዳት ለተረፉና ለሰለባዎች የድጋፍ ደረጃዎችን፣ የምርመረዎችን አያያዝ፣ እና በተግባራዊ ሥራ በሚሰሩ አጋሮች የሚደረጉ ሪፖርቶችን ለማጣጣም የተለዩ ጥረቶች መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. የባለብዙ ወገን ( ሁሉን አቀፍ) ድርጅቶችን በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል እና ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ያላቸውን አቀራረብ ይኸውም በአሁኑ ጊዜ በባለብዙ ወገን ( ሁሉን አቀፍ) ድርጅቶች በማልማት ላይ ያሉትን የአፈጻጸም ግምገማ አውታረመረብ (MOPAN) የልማት እርምጃዎቻቸውን በመደገፍ አፈጻጸማቸውን በጋራ ለመገምገም

ሠ. **ሐብቶችን መወሰን-** የገንዘብና የሰዎች- የዲኤሲ ምክረ ሀሳብ ግቦችን ለመገንዘብና እነዚህን ደረጃዎች ገቢራዊ የሚያደርጉ አጋሮች መደገፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ፡፡

6. **በወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል እና ምላሽ መስጠትን ላይ ለመቆጣጠር ለግምገማ እና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለማዳበር፡-** ለዚህ ውጤታማነት ተከታዮች ማድረግ ያለባቸው፡-

ሀ. ለጥቃት ድርጊቶች የተሰጡ **ምላሾች፣ ድጋፍ፣ እና ክትትል፣ ለማወቅ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎችን ማለትም** ገለልተኛ የአሰራር እድገት እይታክትትል ና **ለግምገማ** እና የተፅዋ ዳሰሳዎች፣ ግምገማዎች፣ ወይም በምርጥ ተሞክሮዎች እና ትምህርት በተማርንባቸው ላይ የግምገማ ዘዴዎች፣ እና ከመግባባት የተደረሰባቸው ትርጉሞችን ማዘጋጀት (ማቋቋም)፤

ለ. **ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችንእና ለተጋላጭ ወገኖች (ቡድኖች) በፆታ እና በዕድሜ የተዘረዘረ መረጃን** ጥራትና መጠንን መለኪያዎች፣ የድርጅቶችንና አጋሮችን ተነሳስሽነቶችን ዳሰሳና ግምገማን ማሻሻል፣ ይህም ለእነርሱ ሚስጥራዊነትን ያረጋግጣል፣ እነዚህ ጥረቶች የተለያዩ ዳታዎችን በሁሉም ድርጅቶች ውስጥ በታትኖ (አሰራጭቶ) ለመጠቀም፣ አቅጣጫዎችን፣ በሌሎች በሁሉም ቦታዎች ክፍተቶችን ለማሳወቅና የመማር አዝማሚያዎችን ለመለያ የሚሆን ጊዜን ሊያካትት ይችላል፡፡

**IV. ዋናውን ጸሐፊ ይህንን የ DAC ምክረ ሃሳብ እንዲያሰራጭ** ይጋብዛል ፡፡

**V. ተከታዮች ይህንን DAC ምክረ ሃሳብ በተለይም በመላው የልማት ፣ በሰብአዊነት እና በሰላም ግንባታ ኤጀንሲዎች እና አጋሮች እንዲሁም በመንግስት ሁሉ እንዲያሰራጩ** ይጋብዛል ፡፡

**VI. ተከታዮች ያልሆኑ ተከታዮች ይህንን DAC ምክረ ሃሳብ እንዲመለከቱ እና እንዲያከብሩ** ይጋብዛል።

**VII. ይህንን የ DAC ምክር ለማስራጨት እና ለመከተል አግባብነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ኢጋሮች ፣ ተቋራጮችን እና የገንዘብ ድጎማዎችን** ያበረታታል።

**VIII. *መመሪያዎች***የ DAC አውታረ መረብ በጾታ እኩልነት ላይ ለ

*ሀ.* ተከታዩች የጋራ ትምህርት እና ማላመድ እንዲደግፉ ፣ እና ለዚህ DAC ማስተዋወቂያ መሳሪያዎችን እንዲያዳብሩ በምክክር ሂደት ፣ በጋራ ፖሊሲዎች ፣ ምርጥ አሰራሮች ፣ እና አዳዲስ አሰራሮችን ወደ ወሲባዊ ጥቃት፣ ብዝበዛና ትንኮሳ መከላከል እና ምላሽ በሚቀርቡ ዘዴዎች ድጋፍ የሚሰጡበት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ መድረክ ይደግፋል ፤

ለ. የዚህን DAC ምክረ-ሀሳብ ተግባራዊነት ይከታተላል ፣ በሥራ ላይ ባለው የ DAC እኩዮች ክወና አሰራር እንዲሁም በሴቶች ፣ በሰላምና ደህንነት ላይ ያሉ እና ለተጨማሪ ክትትልና ግምገማ አማራጮች የሚያዳብሩ ፣ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ግንዛቤን እና ብቃትን ለማጎልበት ትምህርትን ፣ ማላመድን እና ምርጥ ልማዶችን ማጋራትን ይከታተላል ፤ ይማራል ፤

ሐ. የዚህን DAC ምክር ተቀባይነት ካገኘ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እና ከዚያ በኋላ ቢያንስ በየአስር ዓመቱ ለ DAC ሪፖርት ያድርጉ ፡፡

## ታሪካዊ ዳራ

***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳንለማስቆም የተሰጠ የጋራ ምላሽ***

የልማት እርዳታ ኮሚቴ (Dac) ***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***በልማት ትብብር እና በሰብአዊ ዕርዳታ ላይ ለማስቀረት የሚያስችል ምክረ ሀሳብ እ.ኤ.አ. ሐምሌ 12 ቀን 2019 ተቀየሰ ።

የ DAC ምክር በልማት ትብብር እና በሰብአዊ ዕርዳታ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***ላይ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ መሣሪያ ነው ፡፡ ***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***በልማት ትብብር እና በሰብአዊ እርዳታ ሰጪዎች የተፈፀሙ አስደንጋጭሪፖርቶች ምላሽ ለመስጠት የተቋቋመ ሲሆን መንግስታት በለጋሾች ፣ በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ባለድርሻነት ባላቸው አቅም የመደገፍ ፣ የመመራት ፣ የማነሳሳትና የመረዳዳት ፣ የበለጠ ቅንጅታዊ እና ሁሉን አቀፍ እርምጃዎችን የመውሰድ ፣ አለም አቀፍ ደረጃውን የተከተለ ፣ በሚሰጡት እርዳታ ላይ ***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***አደጋ የደረሰባቸውን ሰዎች እና ሰለባዎችን በማስቀደም ፣ የአደረጃጀት ለውጥን በመደገፍ ፣ የአቅም ግንባታን በማጠናከር ፣ የተጠያቂነት አሰራርን እና ለማጎልበት ሰፊ ማእቀፍ ድጋፍ ይሰጣል ፡፡

የ “DAC” ማበረታቻ ለ ‹***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***› ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በጣም ተስማሚ ስርዓቶችን ለመገንባት ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ደረጃን ለማሳየት ያለመ ሲሆን በስድስት ምሰሶዎች ዙሪያ የተገነባ ነው-(i) ፖሊሲዎች ፣ የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃዎች ፣ የድርጅት ለውጥ እና አመራር; (ii) ጥቃትን የተቋቋሙና የጥቃት ሰለባዎችን ማዕከል ያደረጉ የምላሽ እና የድጋፍ ዘዴዎች (iii) የድርጅታዊ ሪፖርቶች, የምላሽ ስርዓቶች እና ሂደቶች; (iv) ሥልጠና ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ግንኙነት; (v) ዓለም አቀፍ ማስተባበር; እና (vi) ክትትል ፣ ግምገማ ፣ የጋራ ትምህርት እና ሪፖርት ማድረግ ፡፡

በተጨማሪም የ “DAC” ማበረታቻ ሃሳብ የ DAC አባላትን እና የ DAC ያልሆኑ አባላትን የያዘውን ቃልኪዳን ተግባራዊ ለማድረግ ፣ ቀጣይ የጋራ መማር ዘዴዎችን ለመዘርጋት እና ለውጡን ለመከታተል በሚያደርጉት ጥረት የተከተሉትን ድንጋጌዎች ያጠቃልላል ፡፡ ወደፊት ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመገንባት ህብትንና ምርምርን በበቂ ሁኔታ ማደራጀት ያስፈልጋል ፤ ይህም ከእነዚህ ጉዳዮች በስተጀርባ ያለውን የኃይል ጉድለትና የፆታ አለመመጣጠን ማስወገድ አስፈላጊ መሆኑን ከግምት ያስገባ ነው ።

የ “DAC” ምክሮች ‹***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን***› በትክክል ትርጓሜ ለመስጠት ባይፈልጉም የተወሰኑ ምንጮች ለህትመት ፣ ለትርጓሜ እና ለትግበራ ጠቃሚ መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡

ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሀፊ የወጡት የተወሰኑ መፅሄቶች - በተባበሩት መንግስታት ስርዓት ውስጥ ***ወሲባዊ ብዝበዛን ፣ ጥቃትንና ትንኮሳን*** ለመከላከል እና መፍትሄ ለመስጠት ለተባበሩት መንግስታት ሰራተኞች ላይ ብቻ ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው ፡፡ በተለይም ፣ በ ‹ST / SGB / 2003/13› ጋዜጣ ላይ የወሲብ ብዝበዛ ማለት “ በተለየ ሁኔታ ተጋላጭ የሆነን የስራ ባልደረባ ወይም በስልጣን የሚያንሰን አልያም የባለደረብነት በእምነትን ያሰደረን ሰራተኛ ለ ወሲብ ጥቅም ጥቃት ማድረስ ወይም መሞከር በዚሁም ድርጊት ቅፅበታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊነ ትርፍን ማግኘትን ያካትተል ፡፡" "ፆታዊ ብዝበዛ" የሚለው አገላለጽ በዚህ ረገድ ሰፋ ያለ ትርጉም አለው ፤ ይህም ሲባል የግብይት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፣ ልቅ የጾታ ግንኙነት የሚፈጽምበትንና ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት የሚበዘብዝበት ነው ማለት ነው ። “የወሲብ ጥቃትን” በተመለከተ ፣ ይኸው መጽሔት "በኃይልም ይሁን እቻ ባልሆነ ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የፆታ ግንኙነት መፈጸም ወይም አካላዊ ጥቃት ማድረስ ማለት ነው" ይላል ።

"ወሲባዊ ትንኮሳ" ን በተመለከተ የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ 'በሴቶች እና በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም ዓይነት ጥቃቶችን ለመከላከል እና ለማስወገድ የተደረጉ ጥረቶችን ማጠናከሩ-ወሲባዊ ትንኮሳ ፣'(A / RES / 73 / 148) "ተግባራቱ በሚፈፀሙበት ግልሰብ ይሁንታ ወይ ተቀባይነት የሌላቸውንና የማይገቡ ባሕሪያትና ልማዶችን ሊያካትት የሚችል ፣ ነገር ግን በፆታዊ አስተያየትና ጥያቄ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ፣ የጾታ ብልግናን ፣ ቃላትን ወይም አካላዊ ድርጊትን ወይም አካላዊ እንቅስቃሴን የሚጠይቁ ፣ እንደ አስጸያፊ ወይም አሳፋሪ ነገር ሊታዩ እንደሚችሉ" ጠበቅ አድርጎ ይገልጻል ።

በመጨረሻም ፣ “ልጆች” የሚለው ቃል በ DAC የውሳኔ ሃሳብ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ፣ የ DAC አባላት “ሕፃናት” ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው የሚል ትርጉም ያለው የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው ፡፡

***የ DAC ምክርን ለማዘጋጀት ሁሉን አቀፍ ሂደት***

እ.ኤ.አ. ሰኔ 2018 (እ.ኤ.አ.) DAC ከአስትሪያ ፣ ከአየርላንድ እና ከእንግሊዝ በመጡ ልዑካን ሰብሳቢነት በ PSEA ላይ DAC የማመሳከሪያ ቡድን አቋቋመ ፡፡ ይህ የማመሳከሪያ ቡድን ከ DAC አባል ልዑካን በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት እና የኢንተር ኤጀንሲዎች ቋሚ ኮሚቴ ተወካዮች ፣ የዓለም ባንክ ፣ ተወካይ የሲቪል-ማህበረሰብ አውታረመረቦች እና DAC አባል ያልሆኑ አገራት ተወካዮችን አካቷል ፡፡

አለማቀፍ ቡድኑ ከሲቪል ማህበራት የእርዳታ ድርጅቶች (CSOs) ጋር ተቀራርቦ ሰርቷል ፣ በ አተገባበር ላይ ከ ዳኬ-ሲኦ ፍሬም ማዕቀፍ ጋር የሚስማማ ሲሆን , የ DAC ምክር በ DAC አባላት እና በ በትብብር አጋሮቻቸው ድርጊቶቻቸውን በ SEA እና SH መከላከል እና ምላሽ ላይ ለማጣጣም የሚረዳ መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል ፡፡ የማመሳከሪያ ቡድኑ በ 2018 ውስጥ ለ DAC አባላት በተላከው ጥልቅ ጥናት አማካይነት ለ SEA እና SH ን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በ DAC አባል ልምዶች ላይ ዝርዝር መረጃዎችን ሠርቷል ፡፡

***አፈጻጸምን መከታተል ፣ ማሰራጨት እና ተከታታይነት ያለው ተግባር ማከናወን***

የ DAC አውታረ መረብ በጾታ እኩልነት (GENDERNET) አሁን ባለው DAC የአቻ ግምገማ ዘዴ በኩል ትግበራውን የሚከታተል ከመሆኑም በላይ DAC ምክር ከተቀበለ በአምስት ዓመታት ውስጥ የበለጠ ተደጋጋሚ ክትትል እና ግምገማ አማራጮችን ያዘጋጃል ፡፡ GENDERNET ከ DAC ከተቀበለ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እና ከዚያ በኋላ ቢያንስ በየአስር ዓመቱ ለአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል ፡፡

## ኮሚቴ (ዎች)

የልማት ድጋፍ ኮሚቴ

## ተዛማጅ መሳሪያ (ዎች)

**ተዛማጅነቱ**

OECD/LEGAL/5019 DAC በሰብአዊ-ልማት-ሰላም ትስስር ላይ የቀረበ ምክር

OECD/LEGAL/0431 ሙስና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ለልማት ትብብር ምክር ቤቱ የሚሰጠውን ምክረ-ሃሳብ

OECD/LEGAL/0418 በሕዝባዊ ሕይወት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ምክር ቤት የተሰጠ ምክረ ሐሳብ

OECD/LEGAL/0398 በትምህርት ፣ በሥራ ስምሪት እና በስራ ፈጣሪነት የፆታ እኩልነት ላይ የምክር ቤቱ አስተያየት